# ለገጠሙት የደህንነት ካሜራ ተመላሽ ገንዘብ ማግኘት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሐብት ይወቁ።

አከራዮች ወይም የንብረት ባለቤቶች ለደህንነት ካሜራ ሲስተም የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት— በዲሲ ውስጥ ላለ ንብረት ውጫዊ ክፍል ለደህንነት ካሜራ ሲስተም ከከፈሉና ከገጠሙ በኋላ ተመላሽ ገንዘብ እናቀርባለን። ተመላሽ ገንዘቡ የሚሸፍነው እያንዳንዳቸው እስከ $200 ለሚሆኑ የካሜራ ዋጋዎች ነው። ከአንድ በላይ ለሆነ ካሜራ ለቤቶች፣ ለከተማ ቤቶች እንዲሁም ለአፓርታማ ህንጻዎች **በመሳሰሉ የመኖሪያ ንብረቶች በድምሩ $500 የሆነ** ተመላሽ ገንዘብ እንዲሁም እንደ ንግድ ተቋማት፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማትን የመሳሰሉ **መኖሪያ ቤት ያልሆኑ ንብረቶች እስከ $750**የሚሆን ተመላሽ ገንዘብ ማግኘት ይችላሉ።

ይህ ፕሮግራም የግል ደህንነት ካሜራ ተመላሽ ገንዘብ የማድረግ ፕሮግራም ሲባል በተጎጂ አገልግሎቶችና ፍትህ እርዳታዎች ቀርቧል።

## ብቁ እንደሆኑ ያጣሩ።

እነዚህ መግለጫዎች **በሙሉ**ትክክል ከሆኑ እርስዎ ብቁ ነዎት፡

- በዲሲ ውስጥ ተከራይተዋል ወይም የራስዎት ንብረት አለዎት። (እያመለከቱበት ያለው ንብረት ዲሲ ውስጥ እስከሆነ ድረስ፣ ከዲሲ ውጪ ሊኖሩ ይችላሉ። ንብረቱ የመኖሪያ ንብረት፣ የንግድ፣ ትርፋማ ያልሆነ ወይም የሃይማኖት ተቋም ሊሆን ይችላል።)
- በዲሲ ውስጥ ከተከራዩት ወይም በባለቤትነት ከያዙት ንብረት ውጪ የደህንነት ካሜራ በ ሴፕቴምበር 22/2015 ወይም ከዚያ በኋላ ገዝተው ገጥመዋል።

ዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እና የተወሰኑ ህዝባዊ ድጋፎችን ካገኙ፣ የ ነጻ የደህንነት ካሜራ ሲስተም ለማግኘትና በዲሲ ውስጥ ባለው ቤት ለመግጠም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ያመልክቱ።

1. እስካሁን ካላመለከቱ፣ ብቁ የሆነ የካሜራ ሲስተም ገዝተው (ተጨማሪ መስፈርቶችን ከታች ይመልከቱ) በተከራዩት ወይም የራስዎ በሆነው ንብረት ውጫዊ ስፍራ ላይ ይግጠሙ። ሲስተሙ

ለ 48 ሰአታት ላሉት ቀረጻዎች ለመያዝ በቂ ማስቀመጫ ሊይዙ ይገባል፣ ይህም ለአንዳንድ ሲስተሞች ተጨማሪ ግዥ ሊሆን ይችላል።

2. ንብረቱን ከተከራዩ፣ ካሜራ ለመግጠም ከአከራይዎ የደብዳቤ ወይም የኢሜይል ፈቃድ ያግኙ።
3. ካሜራዎን(ካሜራዎችዎን) አንላይን የሜትሮፖሊታን የፖሊስ ክፍል (MPD) ጋር ያስመዝግቡ። ይህ ማለት MPD ምርመራ ላይ ድጋፍ ለማግኘት የተቀረጹ ቀረጻዎችን ሊጠይቅዎ ይችላል ነገር ግን ቀረጻዎቹን እንዲያቀርቡ አይጠየቁም። ልክ ሲመዘገቡ፣ ወዲያውኑ የማረጋገጫ ኢሜይል ከመግቢያ ቁጥር ጋር በመሆን ከምዝገባ ሲስተሙ ይደርስዎታል።
4. ለካሜራዎ (ለካሜራዎችዎ) ተቀባዮችን፣ ከ MPD የመግቢያ ቁጥርዎን እንዲሁም ተከራይ ከሆኑ ካከራየዎ ሰው ካሜራዎቹን እንዲገጥሙ የሚፈቅድ ደብዳቤ ይቀበሉ። የእርስዎ የካሜራ ሲስተም በክላውድ ላይ የተመሰረተ ማስቀመጫ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ ለማስቀመጫው እንደሚከፍሉ የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ አለብዎት። ካሜራውን የገጠመልዎ ባለሙያ ከነበረዎት፣ ለእርስዎ ከገጠመልዎት ነጋዴ የተሰጠ ደረሰኝ ማካተት ይችላሉ። (አስፈላጊ አይደለም ነገር ግን የተገጠመውን ካሜራ (ካሜራዎች) ፎቶዎች ከደረሰኙ ጋር ገጣሚዎቹ ካካተቱ፣ ማመልከቻዎን በፍጥነት እናስኬድልዎታለን።
5. የአንላይን ማመልከቻውን ይሙሉ። የማመልከቻ ቅጹን መሙላት ከመጀመርዎ በፊት መለያ መፍጠር አለብዎት። በተጨማሪም ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm ውስጥ በ (202) 727-5124 ላይ በመደወል ማመልከት ይችላሉ።

በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ ወዲያው የማረጋገጫ ኢሜይል ይደርስዎታል። የአይፈለጌ ወይም ስፓም አቃፊዎን ለኢሜይሉ ይፈትሹ። ኢሜይል ካልደረሰዎ፣ እኛን— የዲሲ መንግስት— በ security.cameras@dc.gov ላይ ይጎብኙ ወይም በ (202) 727-5124 ላይ በመደወል ማመልከቻዎ እንደገባ ያረጋግጡ።
2. የካሜራ ሲስተምዎ መገጠሙን በአካል መጥተን እናረጋግጣለን። (ለዚህ ጉብኝት እርስዎ ቤት መገኘት አይጠበቅብዎትም፤ የንብረትዎን የውጪ ስፍራ ብቻ እንፈትሻለን። (የካሜራውዎን ሲስተም በባለሙያ ካስገጠሙ እና ከማመልከቻዎ ጋር ደረሰኝና የተገጠመውን ካሜራ (ካሜራዎች) ፎቶዎች ጋር ከተካተተ፣ በአካል መጥተን ምርመራ ማድረግ አያስፈልገንም።)

3. የካሜራ ሲስተም እንደተገጠመ ካረጋገጥን፣ የማረጋገጫ ኢሜይል ከተመላሽ ዝርዝሮች ጋር አድርገን እንልክልዎታለን። የተመላሽ ቼኩን ለማግኘት እስከ 45 የስራ ቀናት ድረስ ሊወስድ ይችላል።

ካልጸደቀልዎ፣ መቼ እንዳመለከቱ በ 45 የስራ ቀናት ውስጥ በኢሜይል እናሳውቅዎታለን። ካሜራዎቹ በትክክል ባለመገጠማቸው ምክንያት ካልጸደቀልዎ ወይም ማመልከቻዎ መረጃ ጎድሎት ከሆነ ችግሩን ከፈቱ በኋላ እንደገና ማመልከት ይችላሉ።

**ሁሉም ብቁ አመልካቾች ተመላሽ ገንዘቡን ያገኛሉ?**

አይ፣ ለዚህ ፕሮግራም የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በመጀመሪያ ለመጣ፣ በመጀመሪያ ለተገለገለ ነው። ባለፈው አመት፣ ለፕሮግራሙ ብቁ የነበሩ ሁሉም አመልካቾች ተመላሽ ገንዘብ አግኝተዋል።

**ማወቅ ያሉብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**

- ተከራይ ከሆኑ፣ የእርስዎ አከራይ ወይም የንብረት ባለቤት የካሜራውን መገጠም እንደፈቀዱ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ አለብዎት።
- የደህንነት ካሜራ መገጠም ያለበት በቤትዎ ወይም በንብረትዎ የውጪኛው ስፍራ ነው።
- የሁሉም ካሜራዎች ግዴታ፡
  - የአየር ንብረት ተከላካይ
  - ከሚከተሉት ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉትን የቴክኒካዊና የቪዲዮ ጥራት መስፈርቶች ማሟላት፤
    - 1 ሜጋ ፒክስል እና 1280x720 የሆነ የዲጂታል ጥራት ወይም 640X480 የሆነ የአናሎግ ጥራት
    - ደረጃውን የጠበቀ የቪዲዮ ጥራት
    - 5 ፍሬሞች በሰከንድ
  - ቀረጻዎችን ቢያንስ ለ 48 ሰአታት ወይም ለሁለት ቀናት ማስቀመጥ የሚችሉ መሆን አለባቸው

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**

መጀመሪያ፣ በገጹ የታችኛው ስፍራ ላይ ያለውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የተጎጂዎች አገልግሎት እና ፍትህ እርዳታዎች ቢሮን ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm በ(202) 727-5124 ላይ ደውለው ያግኙ። ወይም ቡድኑ ጋር በsecurity.cameras@dc.gov ላይ "የተመላሽ ገንዘብ ፕሮግራም" በሚል ርዕሰ መስመር ኢሜይል ያድርጉ።

**የቤቴን ደህንነት ለመጠበቅ አሁንም እርዳታ ያስፈልገኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?**

በእኛ የቤት ደህንነት ሐብቶች ገጽ ላይ ስለሌሎች ሀብቶች መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**የካሜራ ሲስተም ከመግዛቴ በፊት ማመልከቻ ማስገባት እችላለሁ?**

አይ። ለተመላሹ ያለው ማመልከቻ የካሜራ ሲስተም መግዛትዎን ማረጋገጫ ይጠይቃል። መጀመሪያ የካሜራ ሲስተሙን መግዛት፣ መግጠም እና መመዝገብ አለብዎት (ለማመልከት የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ተከትሎ)።

**የተለየ የደህንነት ካሜራ ሲስተም መግዛት አለብኝ?**

ልዩ የሆነ የደህንነት ካሜራ ሲስተም አይነት ወይም ሞዴል አንጠይቅም ግን እርስዎ የመረጡት የካሜራ ሲስተም አንዳንድ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት (ከላይ ባለው የተጨማሪ መስፈርቶች ላይ እንደተዘረዘረው)።

**የካሜራ ሲስተሜን በክፍያ እቅዱ ላይ ገዝቻለሁ። ለምላሽ ማመልከት እችላለሁ?**

ለካሜራ ሲስተምዎ ሙሉ ክፍያ ከከፈሉ በኋላ ለምላሽ ማመልከት ይችላሉ።

**የደህንነት ካሜራው (ካሜራዎቹ) መገጠም ያለበት የት ነው?**

ካሜራዎቹ ከህንጻው በውጪኛው ስፍራ ላይ መገጠም ይገባዋል።

**ለካሜራ ፍተሻው ቀጠሮ ማስያዝ አለብኝ?**

ምንም ቀጠሮ አያስፈልግም። ካሜራው ከቤትዎ ወይም ከንብረትዎ በውጪኛው ስፍራ ላይ ስላለ፣ በፍተሻ ቦታው ላይ መገኘት አይጠበቅብዎትም።

**የተመላሽ ገንዘቡ የሲስተሙን መግጠሚያና ሌሎች ወጪዎችን ይሸፍናል?**

አይ፣ ተመላሽ ገንዘቡ የካሜራዎቹን ዋጋና የመሸጫ ቀረጥን ብቻ ይሸፍናል። የመግጠሚያ ወጪዎች፣ መለዋወጫዎች እና ማስቀመጫ አልተሸፈኑም።

**ለደህንነት ካሜራ ሲስተም የተመላሽ ገንዘብ ቀድሞውኑ ተቀብያለሁ። እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**
ከከፍተኛው የተመላሽ ገንዘብ ($500 ለመኖሪያ ንብረቶች እና $750 የመኖሪያ ቤት ላልሆኑ ንብረቶች) በታች ከተቀበሉ፣ ካሜራ ወደ ሲስተምዎ ማስገባት ይችላሉ እንዲሁም አዲሱን ካሜራ ለመሸፈን ላለው ተመላሽ ገንዘብ ለማመልከት መመሪያዎቹን ይከተሉ።
በተጨማሪም በዲሲ ውስጥ በተከራዩት ወይም የራስዎ በሆነ የተለየ ንብረት እና እስካሁን ላልተቀበሉት የካሜራ ሲስተም ተመላሽ ገንዘብ ወይም ቫውቸር ማመልከት ይችላሉ።

**ኮምፒውተር ከሌለኝ እንዴት ብዬ ማመልከቻዬን ማስገባት እችላለሁ?**
ማመልከቻዎን በኦንላይን ማስገባት የሚችሉባቸውበመላው ከተማ የኮምፒውተርአቅርቦት የሚሰጡ ብዙ ስፍራዎች አሉ። “FIND” የሚለውን ጽሁፍ ወደ 83224 መላክ ወይም በ (202) CONNECT ወይም (202) 266-6328 ላይ መደወል ይችላሉ።

በተጨማሪም ከማክሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ሰአት ውስጥ በ (202) 727-5124 ላይ በመደወል ማመልከት ይችላሉ።

**የሜትሮፖሊታን የፖሊስ ክፍል (MPD) ካሜራዎቹ ውስጥ ያሉትን ቀረጻዎች መዳረሻ ማግኘት ይችላሉ?**
ተመላሽ ገንዘብ ለማግኘት MPD ጋር የካሜራ ሲስተምዎን ማስመዝገብ አለብዎት። MPD ከካሜራው የቀጥታ ቪዲዮ መዳረሻ አይኖረውም። ለተቀረጹ ቀረጻዎች መዳረሻ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ ነገር ግን ቀረጻዎቹን እንዲያቀርቡ አይጠየቁም።

**ለኮንዶ ህንጻ ማመልከት እፈልጋለሁ። ማመልከቻውን ማስገባት ያለበት ማን ነው?**
ለኮንዶ ህንጻ ማመልከት ከፈለጉ፣ ማመልከቻውን ለማስገባት የኮንዶ ቦርድዎን እንዲጠይቁ እናበረታታዎታለን።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ፌብሩዋሪ 2021 ነው።*